በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ

<u>በያሉበት</u>

ቁጥር / Ref. No. 3-5-0/39/10
ቀን / Date 22 ጥቅምት 2010

ጉዳዩ፡- <u>የኤሌክትሮኒክስ የገቢ ደረሰኝ ጉዳይን ይመለከታል፡፡</u>

የፌደራል ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ ለተገልጋዩ ህብረተሰብ እየሰጠ ያለው አገልግሎት አድማስ እየሰፋ ከመሄዱ ጋር በተያያዘ በየጊዜው የአሰራር ስርዓቱን ማሻሻል /ማዘመን/ እና ተደራሽነቱንም ለማሳደግ ቀደም ሲል በማንዋል የአሰራር ስርዓት ሲጠቀምበት የነበረው የመንግስት ገቢ ገንዘብ አሰባሰብ ስርዓት በኤሌክትሮኒክስ ህትመት /ኮምፒዩተራዝ / ዘዴ ማድረግ እንዲቻል /የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ጠይቆ በተፈቀደለት መሰረት ከመስከረም 1/2010 ጀምሮ በዋናው መ/ቤትና በሁሉም የኤጀንሲው ቅ/ፅ/ቤቶች በዘመናዊ የአሰራር ስርዓት በውስጥ የገቢ ደረሰኝ ህትመት ገንዘብ መሰብሰብ የጀመረ መሆኑን በመግለፅ አዲሱን የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ይዘው ለመገልገል ወደ ባለስልጣኑ ቅ/ፅ/ቤቶች ለሚቀርቡ የህብረተሰብ ክፍሎች /ተገልጋዮች/ ላይ ችግር እንዳይፈጠር አስፈላጊው ትብብር እንዲደረግላቸው በመግለፅ በቁጥር ሰዓ/14/12988 መስከረም 12/2010 በተፃፈ ደብዳቤ ጠይቋል፡፡መረጃው ወደ ገቢ ሰብሳቢ አካላት ከመተላለፉ በፊት ተገቢው ማጣራት የተከናወነ ሲሆን የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ 648/2001 አንቀፅ 10 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ማናቸውም የመንግስት ገንዘብ የሚሰበሰበው ሚኒስቴሩ /የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በሚያሳትመው ወይም እንዲታተም በሚፈቅደው ደረሰኝ ብቻ መሆኑን በግልፅ አስቀምጧል፡፡

በዚህም መሰረት ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተፈቀደበት ደብዳቤ እና የደረሰኙን ዓይነትና ናሙና እንዲልክልን በደብዳቤ ጠይቀን ተልኮልናል፡፡ በመሆኑም ከላይ የተጠቀሰው የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በቁጥር ክሂሡ13/7/3 በ10/08/2009 በተፃፈ ደብዳቤ የፈቀደው ደረሰኝ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዚህ መሰረት በአባሪው የተዘረዘሩት የገቢ ሰብሳቢ አካላት የስራ ክፍሎችና ሰራተኞች ደረሰኙን ለወጪ ማረጋገጫነት ይዘው ለሚቀርቡ ተገልጋዮች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ መሰረት የመንግስት መስሪያ ቤቱ ገቢ እንደሚሰበስብበትና ተፈቅዶ ስራ ላይ ያለ መሆኑን እንዲያውቁት ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የፈቀደበትን ደብዳቤ 1 ገፅ ኮፒ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የሚታተመው ደረሰኝ ናሙና 1 ገፅ ኮፒ አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሰላምታ ጋር//

አባይነሽ አባት
የግብር አወሳሰንና አሰባሰብ አሰራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

<u>ግልባጭ//</u>

- ለፌደራል ሀገር ውስጥ ታክስ ፕሮግራም ልማት ድጋፍ ስራዎች ዘርፍ
- ለአዲስ አበባ ሀገር ውስጥ ታክስ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ስራዎች ዘርፍ
- ለፌደራል አገር ውስጥ ታክስ ጉዳይ ቅ/ፅ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ አዲት አሰራር ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለኢንቨስትጌሽን አዲት ዳይሬክቶሬት
- ለደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት

<u>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን</u>

- ለከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
- ለምሥራቅ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /አዳማ/
- ለሐዋሣ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ሀዋሳ/
- ለባሕርዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ባሀርዳር/
- ለመቀሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /መቀሌ/
- ለድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ድሬዳዋ/
- ለጅማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ጅማ/
- ለኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ኮምቦልቻ/
- ለአዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቁጥር 1 ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቁጥር 2 ቅ/ጽ/ቤት
- ለቦሌ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለአራዳ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለጉለሌ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለቂርቆስ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለየካ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለልደታ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለመርካቶ ቁጥር 1 ጽ/ቤት
- ለመርካቶ ቁጥር 2 ጽ/ቤት

<u>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣ</u>

- ለትግራይ ክልል የገቢዎች ልማት ባለሥልጣን /መቀሌ/
- ለአማራ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ባለስልጣን /ባሕርዳር/
- ለአፋር ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ባለስልጣን /ሠመራ/
- ለደቡብ ብሔር ብሔረሰብና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ባለስልጣን /ሐዋሣ/
- ለሶማሌ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ባለስልጣን /ጅጅጋ/
- ለጋምቤላ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ባለስልጣን /ጋምቤላ/
- ለቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ባለሥልጣን /አሶሳ/
- ለሐረሪ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ባለስልጣን /ሐረር/
- ለድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ኤጀንሲ /ድሬዳዋ/
- ለኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ባለስልጣን /አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance and Economic Cooperation

ቁጥር Ref No ፩/ሺ/ሠ/13/7/3
ቀን Date 10/08/2009

በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
ለፌዴራል የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ
<u>አዲስ አበባ</u>

የአገልግሎት አሰጣጣችሁ ይበልጥ ቀልጣፋ እንዲሆን የገቢ ደረሰኝ ህትመት በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ለማከናወን እንዲፈቀድ በ25/05/09 ዓ.ም በቁጥር ሠማ/14/456 በተፃፈ ደብዳቤ የጠየቃችሁትን ይመለከታል::

የተለያዩ መንግስታዊ ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጣቸውን ይበልጥ ቀልጣፋ፣ ወጪና ጊዜ ቆጣቢ ለማድረግ የኤሌክትሮኒክስ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ እንዲጠቀሙ ይበረታታል::

በዚህም መሠረት በተቀናጀ የፋይናንስ ሥርዓት የሚጠቀሙ የመንግስት መ/ቤቶች የገቢ ደረሰኞችን በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ እንዲያዘጋጁ በመደረግ ላይ ነው::

ስለዚህ ከተቀናጀ የፋይናንስ መረጃ ሥርዓት ጋር የተጣጣመ፣ ተመሳሳይና ወጥነት ባለው መልኩ በጥንቃቄ የገቢ ደረሰኝ ሕትመት በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ እንድትጠቀሙ የተፈቀደ መሆኑን እናሳስባለን::

ከሠላምታ ጋር

ሚኒስትር

ግልባጭ፣
ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
<u>አዲስ አበባ</u>

Letter/tw/

615

242

№ 002082

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር

የገቢ ደረሰኝ

የመንግስት መ/ቤት ስም የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ

ስም አነ አዲሱ አሰፋው

የክፍያ ቀን 5/1/2010

ደረሰኝ ቁጥር 002082

አከፋፈል በጥሬ ገንዘብ

ተ.ቁ	የሂሳብ መደብ	የገንዘቡ መጠን
1	1291	35.00
2	1429	2.00
3	1429	20.00
	ድምር	57.00

የገንዘቡ ልክ በፊደል ሀምሳ ሰባት ብር ብቻ

የገቢ ምክንያት የጠቅላላ ውክልና

samuale worku

የገንዘብ ተቀባይ ስምና ፊርማ